የሰ/መ/ቁ. 62504

ታህሣስ 06 ቀን 2004 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

አመልካች፡- አቶ ታደሰ ናማጋ ሀያቱ - ቀረቡ

ተጠሪ፡- የፌዴራል ፖሊስ ወ/ምርመራ መምሪያ ዋና ሣጅን ደምሴ ሰጠኝ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የአሁኑ ሰበር አመልካች በስር የፌዴራል የመጀመሪያ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረ ሲሆን ተጠሪው ደግሞ ተከሣሽ ነበር፡፡ ክሱም እነዳዊት ጸጋዬ የተባሉት 23 ተከሣሾች ህዳር 27 ቀን 1992 ዓ.ም ከከሣሽ ብር 250,000 ዘርፈው ከተሰወሩ በኋላ በፖሊስ ታድነው በከፊል ተይዘው ክስ የቀረበባቸው ሲሆን በጊዜው ከከሣሽ ዘርፈው ከወሰዱት ገንዘብ ውስጥ ብር 94,000 በኢግዚቢትነት ተከሣሽ ሲይዝ በተረፈው ገንዘብ እነዚህ በወንጀል የተከሰሱ ግለሰቦች ዓይነታቸውን ባላውቅም የተለያዩ የገዙአቸውንም ቁሳቁሶች ጭምር ተከሣሽ በኢግዚቢትነት ይዟል፡፡ ሆኖም በኢግዚቢትነት የተያዙትን ቁሳቁሶች እና ገንዘብ ተከሣሽ እንዲያስረክበኝ ብጠይቅም ለማስረከብ ፍቃደኛ ስላልሆነ ተገዶ እንዲያስረክበኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተከሣሽም በሰጠው መልስ በጊዜው የውንብድና ወንጀል በፈጸሙ 23 ተከሣሾች ላይ 14 ክሶች የቀረቡባቸው ሲሆን በ2ኛ ክስ ከከሣሽ ብር 250,000 ስለመዝረፋቸው በክሱ ተጠቅሷል፡፡ ሆኖም በክሱ ኢግዚቢቶቹ ከ1-8 ተራ ቁጥር ከመዘርዘራቸው በቀር የከሣሽ በኢግዚቢትነት የተያዘው ገንዘብም ሆነ ንብረት ተለይቶ አልተቀመጠም፡፡ በሌላ በኩል በኢግዚቢትነት የተያዙ ንብረቶችን ፖሊስ የመጠበቅ እንጂ የመመለስ ስልጣን የፖሊስ ሳይሆን የፍ/ቤት በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም በሚል ተከራክሯል፡፡

የስር የመ/ደ/ፍ/ቤትም በሰጠው ፍርድ ገንዘቡም ሆነ ሌሎች ቁሳቁሶች የከሣሽ ስለመሆናቸው ከሣሽ ያቀረበው ማስረጃ ካለመኖሩም በላይ ሌሎች ንብረትና ገንዘብ የተወሰደባቸው ሰዎችም ስላሉ ክሱ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

ከፍተኛው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ወገኖች በማከራከር በሰጠው ፍርድ የስር የመ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንቷል፡፡

አመልካችም በስር ፍ/ቤቶች ፍርድ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ሲል አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበ ሲሆን በዋናነት ያቀረበው የቅሬታ ነጥብም፡-

ተጠሪው በስር የመ/ደ/ፍ/ቤት ቀርቦ ከአመልካች ወንበዴዎች የወሰዱትን ብር 94,000 እና በገንዘቡ የተገዙትን ቁሳቁሶች በኢግዚቢትነት መያዙን አምኖ መልስ ሰጥቶ እያለ በማስረጃ አመልካች አላስረዳም መባሉና ክሱ ውድቅ መደረጉ ያለ አግባብ ነው የሚል ነው፡፡
ተጠሪው ለሰበር አቤቱታ መልሱን ያቀረበ ሲሆን በመልሱ ግን በስር ፍ/ቤት ከሰጠው መልስ የተለየ ነገር አላቀረበም፡፡

የግራ ቀኙ ክርክርና በስር ፍ/ቤት የተሰጠው ፍርድ ከዚህ በላይ የተገለጸ ሲሆን እኛም የስር ፍ/ቤቶች በኢግዚቢትነት የተያዘ ገንዘብና ንብረቶች የብዙ የግል ተበዳዮች ስለመሆኑና ከሣሽ የራሱ ገንዘብና ንብረት ነው የሚለውን ለይቶ በማስረጃ ስላላስረዳ ክሱ ውድቅ ነው ያሉት በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የፌዴራል ዐ/ሕግ በ12-7-1993 ዓ.ም በተጻፈ ክስ 14 የወንጀል ክሶችን የውንብድና ወንጀል ፈጽመዋል በተባሉ ተጠሪዎች ላይ አቅርቦ የነበረ ሲሆን የወንጀል ድርጊት ተፈጽሞባቸዋል ከተባሉት የግል ተበዳዮችም አንዱ በ2ኛ ክስ ስሙ የተጠቀሰው ያሁኑ አመልካች ነው፡፡ በክሱም ወንበዴዎቹ ከአሁኑ አመልካች ብር 250,000 ዘርፈው መውሰዳቸው ተገጿል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከክሱ ጋር በተያያዘው የኢግዚቢት ዝርዝር በተራ ቁጥር 3 በወንጀል ክሱ ሶስተኛ ተከሣሽ በ2ኛ እና በ5ኛ ክስ በፈጸመው ዘረፋና የማታለል ወንጀል የገዛው ጃኬት ጫማ ሸሚዝ እና ደብቆ የተገኘው ገንዘብ ብር 48,740 እንዲሁም ስድስተኛ ተከሣሽ በ2ኛ እና በ5ኛ ክስ ላይ በፈጸመው የማታለል እና የዘረፋ ወንጀል ካገኘው ገንዘብ ውስጥ ብር 40,610 እና ከዘረፋው ባገኘው ገንዘብ የተገዛ ሙሉ ሶፋ ፣ ፍሪጅ ፣ ፔርሙስ የመሳሰሉት ንብረት መያዛቸውን ተጠሪው ገልጿል፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የገንዘብ መጠንና ንብረቶች የተያዙት በ2ኛ ክስ በግል ተበዳይነት ከተጠቀሰው ከአሁኑ አመልካች እና በ5ኛ ክስ ከተጠቀሰው የግል ተበዳይ አቶ ገብረማርያም አሰፋ ከተባለ ግለሰብ ነው፡፡ ይህ እስከሆነ ድረስ ደግሞ በኢግዚቢት በተራ ቁጥር 3 እና 4 የተጠቀሰው ገንዘብና ንብረቶች ከሁለቱ የግል ተበዳዮች መካከል በሚደርሳቸውን የገንዘብ መጠንና የንብረት ዓይነት በማጣራት ከመወሰን በቀር በክሱ ውስጥ ያሉ የግል ተበዳዮች ሁሉ ንብረት እና ገንዘብ ነው በማለትና አመልካች ክሱን በማስረጃ አላስረዳም በሚል ውድቅ ማድረግ ስለማይገባ የስር ፍ/ቤቶች ፍርድ ላይ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተናል፡፡
በመሆኑም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት በመዝ.ቁጥር 75346 በቀን 06-7-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመዝ.ቁጥር 92547 በቀን 26-12-2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. የስር የመ/ደ/ፍ/ቤት በ5ኛ ክስ የግል ተበዳይ የሆነውን አቶ ገብረማርያም አሰፋ የተባለውን ግለሰብ ወደ ክሱ እንዲገባ በማድረግ እንዲሁም በጊዜው በወንበዴዎቹ ላይ የተጣራውን የፖሊስ ምርመራ መዝገብ አስቀርቦ በመመልከት ማስረጃዎችን በመመዘን የበኩሉን ፍርድ በጉዳዩ ላይ እንዲሰጥበት ክርክሩን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት እንደገና መልሰናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ